# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

# Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ነሐሴ 15 ቀን 2002 ዓ.ም.**

**ህዝቡ የወያኔ አገዛዝ በቃን ብሎ በካድሬዎች ላይ እርምጃ መውሰድ ጀመረ፤**

**ወያኔ ባለስልጣናቱን ከስልጣናቸው ማንሳት ጀመረ፤**

**ወያኔ ያወጣው እድገት እና ትራንስፎርሜሽን የተሰኘውን እቅድ ነጋዴዎች አጣጣሉት፤**

የሀገሪቱ ህዝቦች ዘር፣ ቀለም፣ ሐይማኖት፣ ቋንቋ ሳይለያያቸው እና ሳይገድባቸው ተከባብረው እና ተፋቅረው ለዘመናት የኖሩትን ክልል በሚል ወያኔ ለአገዛዙ እንዲያመቸው ከፋፍሎ ታሪክና ባህሉን ለማበላሸት ከፍተኛ ጥረት ቢያደርግም ያልተሳካለት ከመሆኑም ባሻገር እስከ ዛሬ ለ19 የግፍና የመከራ ቀንበር ተሸክሞ የነበረውን አገዛዝ ህዝቡ በቃኝ እያለ ምላሽ መስጠት መጀመሩ ታወቀ፡፡

የወያኔ ባለስልጣናት ሰሞኑን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ እያሉ አዲስ ህዝብን የማታለያ ስልት ይዘው በቅስቀሳ ላይ በተሰማሩበት በአሁኑ ወቅት በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የወያኔ አገዛዝ መረረን ያሉ ህዝቦች በካድሬዎች ላይ እርምጃ መውሰድ መጀመራቸው ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በደቡብ ሸዋ ዞን በዱግዳ ቦራ ወረዳ በአርሲ ነገሌ ከተማ አቅራቢያ የሚገኙ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ያሉ ነዋሪዎች የወያኔ ካድሬዎች በተደጋጋሚ የሚያደርሱባቸውን ቅጥ ያጣ አስተዳደራዊ በደልና ፖለቲካዊ ጫና በመቃወም በህብረት በመሆን በወሰዱት እርምጃ አስምት ታጣቂ ሚሊሻዎች እና አንድ የወረዳው ባለስልጣንን ደብድበው ማባረራቸውን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጿል።

እንደ ዘገባው ገለፃ ከሆነ ነሐሴ ወር መጀመሪያ ላይ በአርሲ ነገሌ ከተማ አቅራቢያ የሚገኝ ነዋሪዎች ከአባቶቻቸው ጊዜ ጀምሮ የያዙትን መሬት ለዘመዶቻቸው በመስጠታቸው ካድሬዎች ለምን ትሰጣላችሁ? እኛ ፍቃድ ሳንሰጣችሁ በሚል በማጨናነቃቸው ህዝቡም በንብረታችን ማንም አካል አያዘንም የሚል ምላሽ በመስጠታቸው በተፈጠረ ግጭት ከ11 ሠዎች በላይ ለከፍተኛ ጉዳት መዳረጋቸውን ገልፆል።

በዕለቱ የወረዳው የአህዳዴድ/ወያኔ ጽ/ቤት ኃላፊ 11 ታጣቂ ሚሊሻዎችን አስከትሎ ወደ ስፍራው በመሄድ ያጠሩትን እንዲያፈርሱ ለነዋሪዎች ትዕዛዝ ቢሰጥም አድማጭ በማጣቱ ህዝቡን በዱላ እየተማታ በግድ እንዲያፈርሱ ቢሞክርም በወያኔ የግፍ አገዛዝ ሆድ የባሰው ነዋሪው ህዝብ በህብረት በመሆን በዱላ ሚሊሻዎችንና ባለስልጣኑን ሰባብረው የጣልዋቸው ሲሆን ከሁዋላ የነበሩት ታጣቂዎች የእሩምታ ተኩስ ተኩሰው ከማስጣላቸውም በተጨማሪ አምስት ነዋሪዎችን በከፍተኛ ሁኔታ ማቁሰላቸው ታውቋል።

በገዛ ንብረታችን አዛዥ ናዛዥ አንሻም የሚፈልግብንን ግብር በየጊዜው እየከፈልን ነው በማለት ቁጣ ያሰሙት የቀበሌው ነዋሪዎች በተደጋጋሚ በሚደርስባቸው በደል በመማረር አጋጣሚውን ተጠቅመው ካድሬዎቹን እና ታጣቂ ሚሊሻዎቹን በዱላ ከመደብደባቸውም በላይ የለበሱትን ልብስ አስወልቀው እርቃናቸውን እንዳስቀሩዋቸው ከስፍራው የደረሰን የአይን እማኞችን ዋቢ ያደረገው ዘገባ ገልጿል።

ለሠዓታት ያህል በተደረገው ፍልሚያ ሽንፈትን የተጎነጩት የወያኔ ካድሬዎችና ታጣቂዎች የድረሱልን ጥሪ በማቅረባቸው ከሻሸመኔ የፌዴራል ፖሊሶች መጥተው ከህፃን እስከ አዋቂ ድረስ ምንም ሳይመርጡ በመሳሪያ ሰደፍ እና በዱላ ቀጥቅጠው ከፍተኛ ጉዳት ያደረሱባቸው መሆኑ ታውቋል።

ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ መልኩ ከነዋሪዎች ላይ እያስፈራሩ መሬት እየወሰዱ ሲቸበችቡ የኖሩት የኢህዴድ/ወያኔ ካድሬዎች አሁንም በለመዱት መንገድ እኛ ነን መረከብ ያለብን በሚል ህዝቡን ንቀው በወሰዱት እርምጃ ለውርደት እና ለጉዳት የተዳረጉ ከመሆኑም ባሻገር ህዝቡም እንዲጎዳ ማድረጋቸው ተረጋግጧል።

ግጭቱ ቆሞ የተጎዱት ወገኖች ወደ ህክምና ማዕከል የተወሰዱ ሲሆን፣ እዚያም ሚሊሻዎችና ካድሬዎቹ ብቻ ሲታከሙ ከነዋሪዎች ጉዳት የደረሰባቸው እንዳይታከሙና አፋጣኝ ህክምና እንዳያገኙ ተከልክለው ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት እንደተገደዱ ለማወቅ ተችሏል።

በህዝብ ላብ እና ደም መነገድ የለመዱት የወያኔ ባለስልጣናት በህዝቡ ላይ የደረሰውን ጉዳት እና ጥቃት ወደ ጎን በማለት በካድሬው ላይ በተወሰደው እርምጃ በመቆጨት ከህፃን እስከ አዋቂ፣ ከእርጉዝ እስከ ሽማግሌ፣ ከአሮጊት እስከ አይነ ስውር ሳይቀር በፌዴራል ፖሊሶች እንደተደበደቡ የአይን እማኞችን ዋቢ ካደረገው ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል።

የበሰበሰ እና ያረጀ እንዲሁም የመነቸከ ፖለቲካው በህዝብ ዘንድ እየተጠላ በመምጣቱና ፊት ለፊት መፋለም በተጀመረበት በአሁኑ ሰዓት የህዝቡን ድጋፍ አገኛለሁ በሚል ለመጪው አምስት አመት የሚሆን አዲስ ዕቅድ አውጥቻለሁ እያለ ባዶ ኘሮፓጋንዳ እየነዛ ቢገኝም ሁሉም ህዝቦች በጥርጣሬ እየተመለከቱት መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል::

20 ዓመታትን በህዝብ ጫንቃ ላይ ሲያናጥር አንዳችም የረባ ለውጥ ሳያመጣ ኖሮ ዛሬ ማጣፊያው ሲያጥረው በአምስት አመት ውስጥ ሀገሪቷን ከድህነት ህዝቡን ከልመና አላቅቃለሁ እያለ ቢወተውትም አድማጭ ጆሮ አጥቶ የአዞ እንባ እያነባ መሆኑም ከተለያዩ ስፍራዎች የሚደርሱን ዘገባዎች ጠቁሟል::

በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ነጋዴዎችን ግርማ ብሩና የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ዴኤታ መኮንን ማንያዘዋል የተባሉት ሰብስበው ባወያዩበት ወቅት የንግዱ ማህበረሰብ እንደተሳለቀባቸው የደረሰን ዘገባ ጠቁሞ ካድሬዎች ከመለስ የተሰጣቸውን መመሪያና ትዕዛዝ ለማለት ያህል ብቻ እያሉ እንደሆነ አንጅ እውነት ለውጥ ይመጣል ብለው እንደሚያምኑ ነጋዴዎች በይፋ እንደገለፁላቸው ዘገባው ገልፆል::

አንዳንድ የንግዱ ማህበረሰብ በብስጭት በ20 ዓመት ያልተመዘገበ እድገት በአምስት አመት ተአምር እንሰራለን ማለታችሁ አሳፋሪና አሳዛኝ ቀልድ ነው በማለት የተሳለቁባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ጅቡቲ በአቅሟ በህልውናችን ላይ ስትረማመድ ለማስተካከል አንዳችም ጥረት ካለማድረጋችሁ ባሻገር ተሰሚነታችሁ ሁሉ ባዶ መሆኑን ያሳየ በመሆኑ አምስት ዓመት ስንዴ ልመና እናቆማለን እያላችሁ የሚረዱንን ሀገራት አቅጣጫ ልታስቀይሩ መሞከራችሁ ወንጀል ነው በማለት በንዴት ሲገልፁ ተደምጠዋል::

ግርማ ብሩ አንደበቱ ተሸብቦ ምራቁ ደርቆ ምላሱን ማንቀሳቀስ ተስኖት እንደ መድረክ መሪ ሳይሆን ተሳታፊ መስሎ የዋለ ሲሆን እድሜ ጠገቡ የወያኔ ካድሬ መኮንን ማንያዘዋል በበኩሉ ማብራራት አቅቶት እመኑኝ ሁሉም ያልነው ይፈፀማል እያለ ሲወተውት እንደነበረ ታውቋል::

ከዚሁ ከአዲሱ እቅድ ጋር በተያያዘ የወያኔ ባለስልጣናትን የማንሳቱ ስራ መስከረም ወር 2003 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ይጀመራል ተብሎ የነበረ ቢሆንም ከዛ ቀነ ገደብ ፈጥኖ ሰሞኑን መጀመሩ የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

የሀገሪቷን ህዝቦች እያሰቃየ የሚገኘው ዋና የግፍ መፈፀሚያው የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን የተባለው መ/ቤት ከዋና አዛዡ ጀምሮ ሹም ሽር መጀመሩ ታውቋል::

የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር ሆኖ ለብዙ ዓመታት ሲያገለግል የቆየው ብርሀኑ መልካ (ወደ ሻምበል) ከኃላፊነቱ የተነሳ ሲሆን ሌሎች ሁለት ጄኔራሎችና ሁለት ኮሌኔሎችም ከስልጣናቸው እንዲነሱና በእጃቸው የሚገኙ ንብረቶችን እንዲያስረክቡ መታዘዛቸው ታውቋል::

ሰሞኑን በስልክ በደረሰን ጥቆማ መሰረት ከስልጣናቸው እንዲነሱና ንብረት እንዲያስረክቡ ከፌዴራል ጉዳዮች ሚ/ር ትዕዛዝ የደረሳቸው

1ኛ/ ብርሃኑ መልካ (ወደ ሻምበል) - ምክትል ኮሚሽነር

2ኛ/ ጄ/ል አክሊሉ - የአንድ መምሪያ ኃላፊ

3ኛ/ ጄ/ል አብርሀም ተ/አረጋይ - የአንድ መምሪያ ኃላፊ

4ኛ/ ኮ/ል አብዱልጢፍ - የኮሚሽኑ የህግ ክፍል ኃላፊ

5ኛ/ ኮ/ል አበበ ዘሚካኤል - የቃሊቲ እስር ቤት አዛዥ መሆናቸውም ታውቋል፡፡

እንደ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ከሆነ እነዚህ የወያኔ ሹመኛ ግለሰቦች ምንም እንኳን ካሉበት ቦታ ቢነሱም ለጊዜው ይሁን እንጂ በቀጣይ ሌላ መስሪያ ቤት ውስጥ ሊመደቡ ይችላሉ ሲሉም ግምታቸውን ሲሰጡ ተደምጠዋል፡፡

የዚሁ መስሪያ ቤት ኮሚሽነር የነበረው መኮንን አሰጌ የተባለው ግለሰብ እንደነበር ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጠቁመው ግለሰቡ የወያኔ ቡድን አካሄድ ስላልጣመው በህመም አመካኝቶ ስራውን የለቀቀ ሲሆን፣ በዚያኑ ዘመን ከደራርቱ ቱሉ ጋር በጀመረው ምስጢራዊ ፍቅር አንድ ሴት ልጅ እንደወለደችለትም ምንጮች አስታውሰዋል፡፡

መኮንን አሰጌ የተባለው ግለሰብም የወያኔን ፖለቲካ እርግፍ አድርጐ ትቶ በግሉ እየሰራ እንደሚገኝም ምንጮች ጠቁመዋል፡፡

በአለም ላይ ከፍተኛ እድገት እያስመዘገብኩ ነው እያለ የወያኔ ቡድን እየለፈፈ ባለበት በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ከአለም የመጨረሻ ደሀ ሀገራት ውስጥ ሁለተኛዋ መሆንዋን አንድ የአለም አቀፍ ተቋም አጋለጠ፡፡

በቅርቡ ይፋ በተደረገው አዲስ የድህነት አመላካች ጥናት መሰረት ኢትዮጵያ የአለማችን ሁለተኛዋ ደሀ ሀገር መሆንዋን በይፋ መግለፁ ታውቋል፡፡ የወያኔው መሪ መለስ ሰሞኑን በሰጠው ድንገተኛ ጋዜጣዊ መግለጫ ሳይቀር ያለ አንዳች ሀፍረትና ይሉኝታ ሁለት አሀዝ እድገት በየአመቱ እያስመዘገብን ሲሆን በቀጣዩ አምስት አመት ደግሞ 15 በመቶ እድገት አስመዝግበን ድህነትን ከሀገሪቷ እናባርራለን፣ ሥራ አጥነት ጨርሶ እናጠፋለን እያለ ቢደሰኩርም ያለው ተጨባጭ እውነታ ግን አሁንም በድህነት ከአለም ሁለተኛ ደረጃ ላይ እንደተቀመጠች ጥናቱ ያመለከተ መሆኑ ታውቋል፡፡

በኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ እና በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ኘሮግራም ጥናት ተደርጐ በተዘጋጀው መሠረት ፈርጀ ብዙ የድህነት ችግሮች ተተብትበው ካሉ የአለም ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ ግንባር ቀደም በመሆን የተቀመጠች መሆኑን የአለም አቀፉ ድርጅት ምልከታ አረጋግጧል፡፡

ኒጀርን ተከትላ በሁለተኛነት በድህነት የተቀመጠችውን ሀገር የወያኔ መሪ መለስን ጨምሮ ሌሎች ባለስልጣናት ከህዝቡ እና ከሀገሪቱ እየዘረፉ ኪሳቸውን ያደለቡና ያከማቹት ሀብት እያደገ በሄደ ቁጥር ሀገሪቱዋ ያደገች እየመሰላቸው ባለ ሁለት ድጅት እድገት አስመዘገብን እያሉ ባዶ ኘሮፓጋንዳ እየነዙ ቢሆንም ሩቅ ሳይሄዱ በቅርቡ ውሸታቸው ተጋልጦ የአደባባይ ምስጢር ሊሆን እንደቻለም ታውቋል።

የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ 11 በመቶ በተከታታይ አመታት እድገት አስመዝግበናል እያለ እየወተወተ ቢገኝም አሁን ያለው መሠረታዊ የተባለ የህዝቡ ፍጆታዎች ከመርከስ ይልቅ እየናሩ ከመምጣታቸውም ባሻገር ህዝቡ ቀድሞ ከነበረበት የድህነት አርንቋ ሳይላቀቅ አሁን እየባሰ ወደ አዘቅት እየገባ መሆኑም በገሀድ እየታየ ያለ መሆኑን ታውቆዋል።

የአለም አቀፉ ድርጅት የተለያዩ ጥናቶችን አድርጐ ይፋ ባደረገው ውጤት መሰረት የጤና ችግሮች በህዝቡ ላይ የሚደርሱት ሊቀረፉ ያለመቻላቸው. . . ትምህርት ቤቶች የተሟሉ ያለመሆናቸው... የህዝቡ ኑሮ ከቀን ወደ ቀን እያሽቆለቆለ እንደ ካሮት እድገቱ ወደታች መሆኑና መሠረታዊ ፍጆታዎች እየናሩ መምጣታቸውን በማገናዘብ ኢትዮጵያ የድሆች ደሀ መሆንዋን በጥናቱ አረጋግጧል።

እነ መለስ ዜናዊ ግን በመሳሪያ ኃይል አስፈራርተው የያዙትን ስልጣን ለማጠናከር ሲሉ ብቻ አገሪቱ ፈጣን እድገት እያስመዘገበች ከመሆኑዋም ባሻገር በፈጣን እድገት እየገሰገሰች እንደሆነ የህዝቡን ጆሮ ከሚያደነቁር አሰልቺ ባዶ ኘሮፓጋንዳ እየወተወቱ የሚገኙ ቢሆንም እውነትና ንጋት. . . እንዲሉ ያለው እውነተኛ መረጃ ግን ኢትዮጵያ በፊት ከነበረችበት የድህነት ደረጃ እጅግ በከፋ ሁኔታ ውስጥ መኖርዋን ጥናቱ አጋልጧል።

ሰሞኑን ለሌላ 20 ዓመት የስልጣን ዘመን ማራዘሚያ የሚሆነውን አዲስ የህዝብ ማጭበርበሪያ ዘዴ ነድፎ እድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ እያለ በየስርቻው ነጋዴውን ካድሬውን መምህራኖችን፣ የባንክ ባለሙያዎችን፣ የኢንሹራንስ ባለሙያዎችን እና ሌሎችንም የህብረተሰቡ ክፍሎች አሰልቺ በሆነ መልኩ በግድ ስልጠና እየሰጠ እሙኑ በሚለው በዚሁ ቆርጦ ቀጥል በሆነው መለስ ባዘጋጀው ፅሁፍ ላይ በቀጣዩ 5 ዓመት ድህነት ይጠፋል፣ ስራ አጥነት ታሪክ ሆኖ ይቀራል፣ መሠረታዊ የልማት አውታሮች እጅግ ልዩ ይሆናሉ በሚል እየወተወተ ቢሆንም በአሁኑ ሠዓት ኑሮው ከመሻሻል ይልቅ እየባሰበት ከመሆኑም በተጨማሪ ደሀው ህዝብ በቀን አንድ ጉርሻ መቅመስ አቅቶት በየአውላላ ሜዳው ላይ ሞቶ እንደሚገኝ እየታወቀ እነ መለስ የዓለምን ህዝብ ለማታለል ቁጥር እየደረደሩ መሆኑ የሚያሳዝንና የሚያሳፍር መሆኑንም ዘገባው አብራርቷል።

ሌላው ቢቀር ወያኔ ስልጣን ከያዘ ጊዜ ጀምሮ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የርሀብ ተጠቂ ዜጐች ቁጥር ከመቀነሱ ይልቅ እየጨመረ፣ አስቸኳይ ምግብ እርዳታ የሚፈልገው አትዮጵያዊ ሁለት ድጅት ሚሊዮን እየሆነ መምጣቱ ሀገሪቱ በድህነት አረንቋ ውስጥ እየዳከረች ለመሆኑ ከበቂ በላይ ማስረጃ መሆኑ እየታወቀ እነ መለስ ዜናዊ የሀገሪቱን ስልጣን ብቻ ሳይሆን ሀብትም ጭምር በሚስቶቻቸውና በዘመዶቻቸው ስም በውጭ እና በሀገር ውስጥ ያከማቹት ሀብት መጠን እያደገ በመምጣቱ በራሳቸው ኪስ እያሰሉ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እየተሳለቁ መሆኑን እያሳዩ ነው ሲሉ ስማቸው እንዲገለፅ ያልፈለጉ የምጣኔ ሀብት ባለሙያ በብስጭት ሲገልፁ ተደምጠዋል።

አክለውም እኝሁ ባለሙያ እንዳሉት ከሆነ በአሁኑ ሠዓት ከ6 ሚሊዮን ህዝብ በላይ በአስቸኳይ የምግብ እርዳታ እንደሚፈልግም ይሄንን እንኳ በበጐ ፈቃደኝነት እንስጥ ብለው የገቡትን ለጋሽ ድርጅቶች የተለያዩ ሰበቦችን እየለጠፉባቸው ተገቢ ድጋፍ እንዳያደርጉ እያባረሩዋቸው ነው ካሉ በኋላ የወያኔ ቡድን በመሳሪያ ኃይል በመተማመን ብቻ ለሚሞተው ህዝብ ካለመጨነቁም በተጨማሪ የኢትዮጵያን ህዝብ እንደናቀው የሚያሳይ ነው ሲሉ እንባ እየተናነቃቸው ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡